16ኛ ዓመት ቁጥር 27
16th Year No. 27

ባሕር ዳር ህዳር 15 ቀን 2004ዓ.ም
Bahir Dar November 25, 2011

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

✉ *1324*
*ያንዱ ዋጋ ብር 9.30*
Unit price 9.30

**ማውጫ**

**Content**

**አዋጅ ቁጥር 189/ 2003 ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

**Proclamation No.189/2011**

**A Proclamation Issued to Amend the Amhara National Regional State Income Tax proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 189/ 2003 ዓ.ም

## Proclamation No.189/2011

### በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

### The Amhara National Regional State Income Tax proclamation Amendment Proclamation

በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በሥራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ/ም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ- መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 እና 3/11 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

Whereas, it has become necessary to amend the Income Tax Proclamation No.76/2002, which is in effect in the Amhara National Regional State ;

Now, therefore; the Council of the Amhara National Region, in accordance with the Powers vested with it under Sub-Article 3/1 and 3/11 of Article 49 of the Revised Constitution of the Region, hereby proclaims as follows:

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 189/ 2003 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ማሻሻያ</u>**

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

ሀ/ ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች 19፣ 20 እና 21፣ ተጨምረዋል።

19. "በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ የማስታወቂያ ክፍያ ዘዴ" ማለት ኮምፒዩተራይዝድ የግንኙነት አውታር በመጠቀም የሚፈጸም የማስታወቂያና ክፍያ ስርአት ነው።

20. "የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ" ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ ነው።

21."አቅራቢ" ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ወይም በመሳሪያው ላይ ተጭኖ አገልግሎት የሚሰጥ ሶፍት ዌርን ወይም ሁለቱንም በአንድ ላይ የሚያቀርብ ሰው ነው።

ለ/ የአዋጁ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 11 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 11 ተተክቷል።

11. ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን ለንግድ ስራው ቋሚ ንብረት የተደረገ የጥገና እና የማሻሻያ ትክክለኛ ወጪ እንዲቀነስ ይደረጋል። ወጪው ለእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው የዕቃ ሃያ ከመቶ በላይ ከሆነ ሙሉ በሙሉ በዕቃው የዘመኑ ቀሪ የመዝገብ ዋጋ ላይ ተደምሮ ወጪው በእርጅና ቅናሽ ደንብ መሠረት ይታሰባል።

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Income Tax Proclamation No. 76/2002 Amendment Proclamation No.189 /2011."

2. **<u>Amendment</u>**

The Income Tax Proclamation No.76/2002 is hereby amended as follows:

A. The following new sub Articles 19, 20 and 21 are inserted following sub- article 18 of Article 2:

19. "Electronic Filing and payment system" means a method of e- filing and e- payment made by using a computerized net work.

20. "sales register machine" means a cash register machine or a point of sale machine.

21."supplier" means a person who supplies sales register machines or soft ware which gives service loaded on the cash register machine or supplies both in one to tax payers.

B. Sub- article 11 of article 23 of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub- article 11:

"11. in determination of taxable business income deduction of the actual amount of maintenance and improvement expenses of a business asset is permitted. Where the actual amount of expense is in excess of 20% of the depreciation base of the asset, the whole expense shall be added to the book value of the asset at the year end to increase the depreciation base of the asset.

ሐ/ ከአዋጁ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ/3/፣ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 67 ንዑስ አንቀጽ /3/ና አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ /2/ መጨረሻ ላይ የሚከተለው አዲስ ፓራግራፍ ተጨምሯል።

ግብር ከፋዩ ለባለሥልጣኑ መክፈል ያለበትን ግብር ባለሥልጣኑ በሚወክለው የፋይናንስ ተቋም በኩል ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ በማስታወቅ መክፈል ይችላል። ይህ አሰራር በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ በባለስልጣኑ በሚወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ ይገለጻል።

መ/ በአዋጁ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ /3/ ውስጥ "ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ " የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውስጥ" በሚለው ተተክቷል።

ሠ/ ከአዋጁ አንቀጽ 92 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች 92/ሀ/፣92/ለ/ እና 92/ሐ/ ተጨምረዋል።

**92ሀ/ <u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ</u>**

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፦

1. ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም በባለስልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ መሳሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር ሲጠቀም ከተደረሰበት ለተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሳሪያ ብር 50ሺ. /ሃምሳ ሺ. ብር/ ይቀጣል።

C. The following new paragraph is inserted at the end of sub article 3 of article 52, sub article 3 of article 54, sub article 3 of article 55, sub article 3 of article 67 and sub article 2 of article 68 of the proclamation:

"The tax to be paid to the Tax Authority by the tax payer can be made to financial institution delegated by the tax Authority or through electronically filing and payment system. The Authority by a public notice to be issued shall announce the commencement of such mode of payment."

D. The phrase" With in ten days from the last day of each month" in sub article 3 of Article 54 of the Proclamation is repealed and replaced by "with in thirty days from the last day of each month."

E. The following new sub articles 92a, 92b and 92c are added after article 92 of the proclamation:

**"92a. <u>Penalties for Failure to Meet Requirements of the Use of Sales Register Machines</u>**

Any person who has the obligation to use sales register machines shall be liable for a penalty of:

1. Birr 50,000 if found using sales register machine or point of sales machine software not accredited or registered by the Tax authority;

2. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ገዝቶ መጠቀም ያለበት ሆኖ መሳሪያውን ገዝቶ በመግጠም መገልገል ያልጀመረ ወይም መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም አይነት ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ብር 50 ሺ /ሃምሳ ሺ ብር/ይቀጣል።

3. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ 100ሺ /መቶ ሺ ብር/ይቀጣል።

4. የባለስልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ስርአት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናከል ከፈጠረ ወይም በመሳሪያው ላይ በአመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ካላስደረገ ብር 25 ሺ/ሃያ አምስት ሺ ብር/ ይቀጣል።

5. በንግድ ስራው ለሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው የምርመራ መዝገብ ከመሳሪያው ጐን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም በሽያጭ መመዝገቢያ የተመዘገቡ እቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው ወይም ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡ ሳይረጋገጥ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር 25 ሺ /ሃያ አምስት ሺ ብር/ይቀጣል።

2. Birr 50,000 for carrying out transactions with out receipts or invoice or for using any other receipt not generated by a sales register machine except at the time the machine is under repairer;

3. Birr 100,000 if caused damage to or change of fiscal memory or attempts to cause damage to or change of fiscal memory;

4. Birr 25,000 for obstructing inspection of the audit system of a sales register machine by officer of the Tax Authority or for failure to have annual machine inspections performed by a service center;

5. Birr 25,000 for not having a valid service contract with an authorized service center for a sales register machine in use, or for using the sales register machine with out connecting to the terminal, for not keeping the inspection booklet besides the sales register machine, or for issuing refund receipts with out properly recording the return of goods or customers' request for refund in the refund book;

6. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው በስርቆት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በሶስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ብልሽት ቢጋጠመው በሁለት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 10 ሺ. /አስር ሺ. ብር/ ይቀጣል።
7. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚቀመጥበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር 50 ሺ. /ሃምሳ ሺ. ብር/ይቀጣል።
8. የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደርግ ወይም የንግድ ስራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ከሶስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለስልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር 25 ሺ. /ሃያ አምስት ሺ. ብር/ ይቀጣል።
9. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ጥቅም ላይ በሚውልበት የንግድ ስራ ቦታው፦
   ሀ/ የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ የንግድ ስራ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን የእውቅና እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣
   ለ/ የሽያጭ ሠራተኞች መሳሪያው የተበላሸ ከሆነ በባለስልጣኑ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኛው የመስጠት ግዴታ አለባቸው/ የሚል ማስታወቂያ፣ እና
   ሐ/ ደሰረኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ/ የሚል ጽሁፍ ያለበት ማስታወቂያ፣ በግልጽና በሚታይ ቦታ ለጥፎ ካልተገኘ ብር 10 ሺ. /አስር ሺ. ብር/ ይቀጣል።

6. Birr 10,000 for failure to inform the Tax Authority and the machine service center with in three days of the termination of a sales register machine use due to theft or irreparable damage, or with in two hours for failure to report machine malfunction due to any other causes;

7. Birr 50,000 for failure to notify the Tax Authority the correct place of business the sales register machine is in use;

8. Birr 25,000 for failure to notify the Tax Authority change of name of address or for failure to notify the Tax Authority and service center three days in advance in cases of termination of business;

9. Birr 10,000 for failure to put a conspicuous notice containing one or all the following information at a place where the machine is installed:
   a. name of the machine user, trade name, location of trade, tax payers identification number, accreditation and permit numbers for the sales register machine;
   b. text stating that “in case of machine failure sales personnel must issue manual receipts authorized by the Tax Authority”;
   c. text that reads “Do not pay if a receipt is not issued”.

10.ሥራ ላይ የዋለውን የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር ባለስልጣኑ እውቅና ባልሰጠው ሰው እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ካደረገ ብር 30 ሺ. /ሰላሳ ሺ. ብር/ ይቀጣል።

## 92 ለ/ የአቅራቢነት ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅናና ፈቃድ የተጠሰው ሰው፦

1. የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 100 ሺ. /መቶ ሺ. ብር/ይቀጣል።
2. በባለስልጣኑ እውቅና ያልተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ለገበያ ካዋለ ብር 500 ሺ. /አምስት መቶ ሺ. ብር/ ይቀጣል።
3. ለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ምዝገባ ከባለሥልጣኑ የመሳሪያ መለያ ቁጥር ካልወሰደ ወይም የወሰደውን የመሳሪያ መለያ ቁጥር ለእይታ በሚያመች ቦታ በመሳሪያው ላይ ካለጠፈ ብር 50 ሺ. /ሃምሳ ሺ. ብር/ ይቀጣል።
4. በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም ስለመሳሪያው አጠቃቀም በሚያብራራው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ብር 100 ሺ. /መቶ ሺ. ብር/ ይቀጣል።
5. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በመሰረቃቸው ወይም ሊጠገኑ በማይቻልበት ሁኔታ በአደጋ ምክንያት ብልሽት የደረሰባቸው መሆኑን አስታውቀው እንዲተኩላቸው ለሚጠይቁ የአገልግሎት ማዕከላት በሶስት ቀናት ውስጥ ለማቅረብ አለመቻሉን ለባለሥልጣኑ አስቀድሞ ካላሣወቀ ብር 50 ሺ. /ሃምሳ ሺ. ብር/ ይቀጣል።

10. Birr 30,000 for changing or improving a point of sales machine soft ware by a person not accredited by the Tax Authority.

## 92b. Penalties for failure to observe Supplier's Obligations

Any person who is accredited and permitted for the supply of sales register machine or soft ware shall be liable for a penalty of:

1. Birr 100,000 for failure to notify change of business address to the Tax Authority;
2. Birr 50,000 for selling a sales register machine not accredited by the Tax Authority;
3. Birr 50,000 for failure to get a machine registration code for each sales register machine from the Tax Authority or for not affixing the machine code stickers on a visible part of the machine;
4. Birr 100,000 for failure to notify to the Tax Authority in advance any change made to the sales register machine in use or for inserting or adding incorrect information or for omitting the correct information from the manual that guides the use of sales register machine;
5. Birr 50,000 for failure to notify the Tax Authority in advance or for not being able to replace, with in three days of the request made by a service centre, sales register machine lost due to theft or sustained irreparable damage;

6. ውል ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ውላቸውን ስላቋረጡ ወይም አዲስ ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት ለባለስልጣኑ ካላሣወቀ ብር 50 ሺ. /ሃምሳ ሺ. ብር/ ይቀጣል።

92 ሐ/ **<u>የአገልግሎት ማዕከላት ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ</u>**

ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል፦

1. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የፊሲካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ካላሣወቀ ብር 20 ሺ. /ሃያ ሺ. ብር/ ይቀጣል።
2. ውል የገባባቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላስደረገ ብር 20 ሺ. /ሃያ ሺ. ብር/ ይቀጣል።
3. አቅራቢው ዕውቅና ሳይሰጠውና በባለሥልጣኑ ዘንድ ሳይመዘገብ በስራ ላሰማራው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር 50 ሺ. /ሃምሳ ሺ. ብር/ ይቀጣል።

ረ/ ከአዋጁ አንቀጽ 98 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች 98ሀ፣ 98ለ፣ እና 98ሐ ተጨምረዋል።

98 ሀ/ **<u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት ስለሚፈጸም ጥፋት</u>**

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፦

1. በባለሥልጣኑ እውቅና ያልተሰጠው ወይም ያልተመዘገበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከተጠቀመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፣

6. Birr 50,000 for failure to keep information about service centers with which it has signed agreements or for failure to notify the Tax Authority about contracts terminated or newly entered agreements with service centers.

92 **<u>c. Penalties failure to observe Sales Register Machine Service Centers, obligation</u>**

Any Sales Register Machine Service Center shall be liable for a Penalty:

1. Birr 20,000 for failure to report the Tax Authority with in two days of change of the fiscal memory of a sales register machine;
2. Birr 20,000 for failure to perform annual technical inspections on sales register machines that are under contract;
3. Birr 50,000 for deploying every person not certified by the supplier and not registered by the Tax Authority.

F. After Article 98 of the proclamation the following new Articles 98a, 98b and 98c are added:

98 **<u>a. Violations of the Requirements of the use of Sales Register Machines</u>**

Any person who has the obligation to use sales register machine:

1. commits an offence if found using a sales register machine not accredited or registered by the Tax Authority and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;

2.የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም ያለበት ሆኖ መሳሪያውን ገዝቶ በመጠቀም መገልገል ያልጀመረ ወይም መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፣

3.በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው የፊሲካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

4.የባለስልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል የፈጠረ ወይም በመሳሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ያላስደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

5.የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው የሚገኝበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

### 98 ለ/ <u>በአቅራቢዎች የሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት እውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፦

2. except at the time the sales machine is under repair, commits an offence if carried out transactions with out receipt or invoice or used any other receipt not generated by a sales machine and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;

3. commits an offence if caused damage or change to the fiscal memory of a sales register machine or attempts to cause damage or change to the fiscal memory and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years;

4. commits an offence if obstructed inspection of the audit system of a sales register machine by officer of the Tax Authority, or if failed to have annual machine inspections performed by a service center and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not lea than six months and not more than one year;

5. Commits an offence if failed to notify to the Tax Authority the correct business address where a sales register machine is in use and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than six months and not more than one year.

### 98 <u>b. Offences by Suppliers</u>

Any person who is accredited and registered to supply sales register machines:

1. የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።
2. በባለሥልጣኑ እውቅና ያልተሰጠውን መሳሪያ ለገበያ ካዋለ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።
3. በስራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለባለስልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም በመሳሪያው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

**98ሐ/ <u>በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የአገልግሎት ማዕከልና ሠራተኞች የሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>**

1. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል አቅራቢው እውቅና ያልሰጠውንና በባለስልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ ሠራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሶስት አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

1. Commits an offence if failed to report to the Tax Authority a change of business address and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;
2. Commits an offence if sold a sales register machine not accredited by the Tax Authority and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years;
3. Commits an offence if failed to notify the Tax Authority in advance any change made to the sales register machine in use, or if inserted incorrect information to or omitted the correct information from the manual that guides the use of sales register machine and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years.

**98 <u>c. Offences by Sales Register Machine service Centers and their personnel</u>**

1. Any sales register machine service center commits an offence if deployed a service personnel that is not certified by the supplier and not registered by the Tax Authority and shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years;

2. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ያለአገልግሎት ማዕከሉና ያለባለሥልጣኑ እውቅና ከፈታታ ወይም ከገጣጠመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሳይበላሽ ሆን ብሎ እሽጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ አድራጐቶች ከፈጸመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5 ሺ /አምስት ሺ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

ሰ/. የአዋጁ አንቀጽ 100 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 100 ተተክቷል።

**100. <u>በባለሥልጣኑ ሠራተኞች የሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>**

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም በባለሥልጣኑ የተቀጠረ ማንኛውም ሰው፦

ሀ/ በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባው ክፍያ ወይም ሽልማት ወጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ አይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ወይም ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣

2. Any personnel for a sales register machine service center commits an offence if, with out the knowledge of the service centre and the Tax Authority, dismantle or assemble a sales register machine, or if deliberately removed the seals on the sales register machine or changed parts of a sales register machine not reported to have any break down, or if committed any similar act and shall, up on conviction, be punished with a fine of not more than Birr 5,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

G. Article 100 of the proclamation is repealed and replaced by the following new Article 100.

**100. <u>Offences committed by Employees of the Authority</u>**

1. Any person employed by the Tax Authority for enforcing the provisions of this proclamation who:

a. In connection with any of his duties, directly or indirectly asks for or receives a payment or reward, whether pecuniary or other wise, or promise or security for that payment or reward, not being a payment or reward to which he is lawfully entitled to receive;

ለ/ ከግብር በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈጻጸም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈጸም፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በግብር ላይ የሚፈጸምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ እንደሆነ ወይም፣

ሐ /በዚህ አዋጅ ለባለስልጣኑ ከሰጠው ሥልጣን በላይ የሰራ ወይም በተሰጠው ሥልጣን ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ፣ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50 ሺ /ሃምሳ ሺ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአስር አመት በማያንስ ከሃያ አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

2. የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች አጠቃቀም ደንብና መመሪያዎችን በመተላለፍ፦

ሀ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የፈታ ወይም የገጣጠመ ወይም የአገልግሎት ማዕከል ሰራተኛ በሌለበት ስራ ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም የመሳሪያውን መለያ ቁጥር ያቀያየረ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚው ወይም በአገልግሎት ማዕከሉ ወይም በሰራተኛው ወይም በአቅራቢው የተፈጸመን ማናቸውንም ሕገ ወጥ አድራጐት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5 ሺ/አምስት ሺ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

b. Enters into or acquiesces in an agreement to do or to abstain from doing any thing, or to permit, conceal connive at any act where by the tax revenue is defrauded or which is contrary to the provisions of this proclamation or to the proper execution his duty; or

c. Exceeds the power conferred up on the Tax Authority or misuses such authority; Commits an offence and shall, up on conviction, be punished with a fine of not more than Birr 50,000 and imprisonment for a term of not less than 10 years and not more than 20 years.

2. Any employee of the Tax Authority who, in violation of the rules and procedures of the use of sales register machines:

a. Dismantles or assembles a sales register machine or approves its utilization with out the presence of a service personnel or changes the machine registration code; or

b. Knowingly or negligently fails to report the Tax Authority, with in 24 hours, offences committed by the user, service center or its personnel or supplier of a sales register machine; Commits an offence and shall, up on conviction, be punished with a fine of not more than Birr 5,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

3. የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለበቂ ምክንያት ጉዳይን በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሃብሔር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

ሸ/ የአዋጁ አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ /1/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /1/ ተተክቷል፡፡

1. የይግባኝ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የይግባኝ ጉባኤው የጽሁፍ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ቀ/ የአዋጁ አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሽሯል፡፡

በ/ የአዋጁ አንቀጽ 115 ንዑስ አንቀጽ /1/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /1/ ተተክቷል፡፡

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አባላት የንግዱን ህብረተሰብ ተወካዮች ጨምሮ በሕዝብ ዘንድ ባላቸው ታዋቂነትና ታማኝነት፣ ባላቸው ጠቅላላና ልዩ እውቀት፣ እንዲሁም ከግብርና ቀረጥ ጋር በተገናኘ ጥፋት ካልፈጸሙ ሰዎች መካከል ተመርጠው ይሰየማሉ፡

3. The Tax Authority's Officer shall be held responsible for any damage caused to a tax payer by delaying with out any good cause, the performance of his/her duty. Such officer in addition to being held liable for the damage, shall, up on conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years.

H. Sub- article1 of Article 113 of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub- article 1:

"1. Any party dissatisfied with a decision of the appeal commission, on the ground that it is erroneous on any matter of law, may appeal to the competent court of appeal of the written decision of the appeal commission."

2. Sub- article 4 of article 113 is hereby repealed.

i. Sub- article 1 of article 115 of the proclamation is repealed and replace by the following new sub- article1:

"1. Members of Appeal Commission at every level shall be appointed from among persons, including representatives of business communities, having good reputation, acceptability, general and professional knowledge, and who have not committed any offence in connection with tax and tax administration."

ተ/ ከአዋጁ አንቀጽ 115 ንዑስ አንቀጽ 4 ውስጥ "ከዚህ በላይ በአንቀጽ 114 /3/ ከተዘረዘሩት መካከል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ከተዘረዘሩት መካከል" በሚለው ተተክቷል።

ቸ/ የአዋጁ አንቀጽ 115 ንዑስ አንቀጽ 6 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 ተተክቷል፡

የማንኛውም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አባል የአገልግሎት ዘመን ለሁለት ዓመታት ጊዜ ይሆናል። በይግባኝ ጉባኤ ወይም በጉባኤው ችሎት በሰብሳቢነት እንዲያገለግል የተመረጠ ሰው የስራ ዘመን ለሁለት ዓመት ወይም በምትክነት የተመረጠ ሲሆን የተካው ሰው ለቀረው የስራ ጊዜ ይሆናል። ከሁለት ዓመት በላይ የሰራ የጉባኤ አባል እንዳስፈላጊነቱ በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡

j. The phrase "by appropriate entities listed under article 114(3) under sub- article 4 of Article115 is repealed and replaced by the phrase "by the appropriate organs from among persons referred to in sub- article 3 of this article."

L. Sub- article 6 of article 115 of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub article 6:

"the term of office of a member of an Appeal Commission shall be for two years. A member appointed to chair an Appeal Commission or a panel of the Commission shall serve in that capacity for two years or the remaining period of that other member's term if he is a substitute. Where necessary, any member of an Appeal Commission may be assigned for another term of office."

## 1. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

## 2. Effective Date

This proclamation shall enter in to force as of its publication in the Zikr- Hig Gazette of the Regional State.

ባህር ዳር
ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም
አያሌው ጐበዜ,
የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

Done at Bahir- Dar
This 25th day of November, 2011
Ayalew Gobezie
President of the Amhara National Region